**በማተቡ፡ በእምነቱ ጸንቶ፤ ስለእምነቱ ኖሮ በእምነቱ ያለፈ አንጋፋ ኢትዮጵያዊ**

**አቶ ሹምዬ ተፈራ አባሚርጎ**

"በማተቡ!!" አላቸው ለሀያ ዓመት አካባቢ የሚያውቃቸው አቶ ጥጋቤ።

"ከዚያ ሁሉ እሳት ውስጥ ይወጣል ብሎ የገመተ የለም" አሉኝ፡ ታናሽ እህታቸው ወ/ሮ አስናቀች ተፈራ እና የረጅም ግዜ የትግል አጋራቸው አቶ ወልዴ።

"እኔ ምንም የምናገርበት አንደበት የለኝም። በህይወቴ፡ ከሱ ጋር ከተገናኘሁ ጀምሮ አርቲፊሻል ሳይሆን፡ እውነተኛ ፍቅር፡ በቤተሰቦቼም፡ በጓደኞቼም ዘንድ ሀይለኛ አክብሮትና ፍቅር እንዳለኝና እንዳገኘሁ ብቻ እንጂ። ከተገናኘንበት ግዜ ጀምሮ ጸባዩ አንደበቱ ቋንቋው ሳይቀየርብኝ፡ እንዳገኘሁት የተለየሁት፡ የህይወት አጋሬ፡ ትዳሬ፡ ጋሻዬ ነው። በትዳር ዘመናችን አንድም ቀን ሽምግልና ገብቶብን አያውቅም። እኔ ብዬ ወይም ጠይቄ አንድም ቀን ከልከሎች፡ እንቢኝ ብሎ የማያውቀውን ባሌን ነው ያጣሁት" አሉ ባለቤታቸው ወ/ሮ ጂጂ ይገዙ።

ይሄ ብቻ አይደለም። "በቀይ ሽብር ሰው በተገደለ ቁጥር፡ እሱ ነው እያልኩ፡ ሬሳ ስቆጥር እውል ነበር። ሞቷል፡ የቀበሌ አመራሮች ነጻ እርምጃ እንዲወስዱ ስልጣን በተሰጣቸው ሰዓት፡ ከዚያ ተርፎ ይወጣል ብዬ አልገመትኩም። ከዚህ ሞት ተርፎ ሌላ ቦታ ሞተ ብባል ግን አላለቅስም ብዬ ቃል ገባሁ።" ያሉትና ለስድስት ዓመታት ሞቷል ብለው እርማቸውን አውጥተው፡ ጥቁር ለብሰው የኖሩት፡ አሁን ግን እንኩዋንስ እሳቸውን ማናችንንም ያስደነገጠን ድንገተኛ ሞታቸው የከፈተውን ልቅሷቸውን ሊገቱ ያልቻሉት ወ/ሮ አስናቀች፡ ከሀያ ዘጠኝ ዓመት መለያየት በኋላ ያገኟቸውና አይተውም ያልጠገቧቸው ወንድማቸውን ለመጨረሻ ግዜ ያዩዋቸው ከመሞታቸው አንድ ሳምንት ቀደም ብሎ ነበር። ይሄ ባለፈው ቅዳሜ ባስደንጋጭ መልኩ የተቋጨው የወንድማችን፡ የአባታችን፡ የአጋራችን የአቶ ሹምዬ ተፈራ የሕይወት ጉዞ የዛሬ ስልሳ ስድስት ዓመት ነበር የጀመረው። መስከረም፡ የከተራ እለት።

አቶ ሹምዬ ተፈራ፡ ከአባታቸው፡ ከአቶ ተፈራ አባሚርጎ፡ ከእናታቸው ወ/ሮ ጌጤ ቱሉ፡ እንደ አበሻ አቆጣጠር፡ መስከረም 16 ቀን፡ ሺህ 9 መቶ 35 ዓ.ም.፤ በሸዋ ክ/ሀገር፡ ከአዲስ አበባ ወጣ ብላ ከምትገኘው፡ ሙሎ ከተማ ከጭቁን ቤተሰብ ተወለዱ። አባታቸው በልጅነታቸው በሞት ስለተለይዋቸው፡ እድሜያቸው ለትምህርት ሲደርስ፡ እናታቸው ወደአዲስ አበባ አምጥተዋቸው፡ የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርታቸውን፡ በአርበኞች አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተማሩ። የሁተኛ ደረጃ ትምህርታቸውን ደግሞ በመድሀኔዓለም ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት አጠናቀቁና በመጀመሪያ ያኔ ኢንዶ ቴክስታይል፡ አሁን አቃቂ ቴክስታይል ፋብሪካ ውስጥ ተቀጠሩ። እዚያ ነው የአቶ ሹምዬ ተጋድሎ የሚጀምረው። እኚያ ከኛ ጋር እንደ ተራ ሰው ሲመላለሱ የነበሩት አቶ ሹምዬ፡ በሂልተንም ሆቴልም ይሁን በኢንዶ ጨርቃጨርቅ በተለይ ለሰራተኛው የዋሉትን ውለታ ሲጠቅሱ፡ የስራ ባልደረባቸው ሲቃ እያነቃቸው ነበርና አምስት ስድስት ግዜ ውይይታችንን ማቋረጥ ነበረብን። በአቃቂ ጨርቃጨርቅ ካከናወኗቸው ተግባራት ውስጥ፡ በረጅም ግዜ የትግል አጋራቸው አነጋገር የሚከተሉት ይገኙበታል።

በ1960ዎቹ መጀመሪያዎቹ ላይ፡ በአቃቂ ኢንዶ ቴክስታይል ፋብሪካ ውስጥ የነበረውን አሰቃቂ የስራ ሁኔታ፡ ማለትም ሰራተኛው ምንም አይነት መፈናፈኛ በሌለበት፡ በጥጥ ብናኝ ሳምባው እየተሞላ በሚሰቃይበት ጊዜ፡ ያ መወገድ አለበት አሰሪዎች ለሰራተኛውም የተሻለ የስራ ሁኔታ ሊፈጥሩ ይገባል በሚል ጽኑ እምነት፡ ህይወቱን ለኢትዮጵያ ሰራተኞች ማህበር ለመስጠት ወስኖ የተነሳ የጊዜው ወጣት የኢትዮጵያ ሰራተኞች መሪ ነበሩ። በዚህም ጽኑ እምነታቸው፡ የተነሳ ለ3 አመት

የኢንዶ ቴክስታይል ሰራተኞች የስራ ሁኔታ (working condition) እንዲሻሻል ብዙ መስዋእትነትን የከፈሉ ሰውና በዚህም ቆራጥ ትግላቸው፡ ለኢንዶ ቴክስታይል ሰራተኞች አመርቂ ውጤቶችን ያስመዘገቡ የሰራተኞች መሪ ነበሩ። በሳቸው ቆራጥና አይታክቴ ጥረት የሰራተኛው መብት እንዲሻሻል የተሻሉ የህብረት ስምምነቶችን ያስገኙ ፍጹም ሰራተኛ አፍቃሪ ላብ አደርና ለዲሞክራሲና ለፍትህ የበላይነት የቆሙና በጽናት የታገሉ፡ በጽናት የመሞት ሕይወትን፡ የህይወቱና የትግል ዝማሬያቸው ያደረጉ ኢትዮጵያዊ ነበሩ።

ያኔ በአቃቂ በሰቃ፡ ትርፋቸው ብቻ የሚያንገበግባቸው የህንድ ባለሀብቶች፡ በተለይ ሴቶች ሰራተኞች በጥቂት ወጪ መከላከያ መከላከል ይቻል በነበረ የኢንዱስትሪ ብናኝ፡ በየቀኑ በሳንባ ነቀርሳ ሲረግፉ፡ “ይሄንንስ ቆሜ አላይም ብለው፡” ያንን በማስቀየር የሰራተኛው መብት እንዲጠበቅ አድርገዋል። በወቅቱ ከህንድ የፋብሪካው ባለሀብቶች ጉቦ የሚበሉ የንጉሱ ሚኒስትሮችና ባለሚሎች የሰራተኛው መብት እንዳይጠበቅ ብዙ ተጽእኖና ማስፈራሪያ ቢያደርጉባቸውም፡ አቶ ሹምዬ ግን እስከመጨረሻው ያንን ተቋቁመው ለውጥ አምጥተዋል።

ይሁን እንጂ፡ ይላሉ ጓደኛቸው፡ “አቶ ሹምዬ ተፈራ በነበረው ቆራጥና ቅን የሰራተኛው መብት ተከራካሪነቱ የተነሳ፡ እስከጠቅላይ ሚኒስትሩ በደረሰ ከአሰሪዎችና የመንግስት ተወካዮች የተደረገ የክስ ሂደት በተላለፈ ትእዛዝ፡ የኢንዶ ቴክስታይል(አቃቂ ጨርቃጨርቅ) ስራውን እንዲያጣ ተደረገ። የአቶ ሹምዬ ተልእኮ ግን አላበቃም ነበርና፡ ከአቃቂ ቴክስታይል በመንግስትና በአሰሪዎች ትእዛዝ ከስራቸው ሲባረሩ በአዲስ አበባ ሂልተን ሆቴል በሂሳብ ሰራተኝነት ተቀጠሩ። እሳቸው፡ የሰራተኛው ቦርድ አባል ሆነው እንዲሰሩ ተመርጠው ሲያገለግሉ፡ በሰራተኛና በአሰሪ መካከል ባለው ውጥረት አለማቀፋዊ ልምድ ያለው የሂልተን ተወካይ ተጠርቶ፡ ይህ አለማቀፋዊ ልምድ አለው የተባለው የአሰሪዎች ተወካይ 23 የቦርድ አባላትን ሰብስቦ ስኮላር ሺፕ፡ ሹመት፡ የደመወዝ እድገት አግኝታችሁ ብትኖሩ ይሻላችኋል ብሎ ባቀረበው ማባበያ፡ ከ23ቱ የቦርድ አባላት 3ቱ ብቻ ሲቀሩ፡ የተቀሩት የሰራተኞችን ማህበር፡ አፍርሰው ሲሄዱ፡ በወገኖቹ ላይ መደራደር የማይዋጥለት አቶ ሹምዬ ግን፡ እነዚህን 3 ግለሰቦች ይዞ በውድቅት ጨለማ ሰራተኛውን በንግድ ስራ ት/ቤት አዳራሽ ሰብስቦ፡ እሱ በሊቀመንበርነት ሲመረጥ፡ የቦርድ አባላቱን አሟልቶ የሰራተኛው መብት እንዲከበር ያደረገ ቆራጥና ጀግና ታጋይ ነበር። በዚህም የተነሳ ሲገባ ሲወጣ፡ በቀን ከ3-5 ጊዜ እንዲፈርምና ተስፋ ቆርጦም ስራውን እንዲያቆም ቢደረግም በነበረው ጽኑ እምነትና ቆራጥ አላማ ስራውን ቀጥሎ፡ በሰራተኞችና በአሰሪዎች መካከል የጋራ ስምምነት እንዲፈረም ያደረገ በጽናት ትግል የሚያምን ሰው ነበር።

የአቶ ሹምዬ ታሪክ እንዲህ አጭር አይደለም። አቶ ሾምዬ በሂልተን ሆቴል የሂሳብ ሹም ሆነው ተቀጥረው ሲሰሩ በነበረበት ጊዜ፡ የሰራተኛው ተወካይ መሪ ሆነው ሲያገለግሉ የሂልተን ሆቴሎች አለማቀፋዊ የሆኑ የሰራተኛው ጥቅሞችና መብቶችን፡ በመመርመርና እነዚያ ግድፈቶች እንዲታረሙ አድርገዋል። በአዲስ አበባ ሂልተን ሰራተኞችና በአለማቀፍ የሂልተን ሰራተኞች መካከል በነበረ እኩልነት የሌለበት አሰራር፡ የኢትዮጵያ ሂልተን ሰራተኞች የአገልግሎት ክፍያ ሳይከፈላቸው፡ በአለማቀፍ የሂልተን ሰራተኞች ግን ቋሚ ህግ ሆኖ ይከፈላቸው እንደነበር በማረጋገጥ፡ የኢትዮጵያ ሂልተን ሰራተኞችም የዚህ አለማቀፍ የሰራተኞች መብት ተጠቃሚ መሆን አለባቸው በማለት ተከራክረው፡ በወቅቱ ያገኙት መልስ “የኢትዮጵያ ሆቴሎች በሙሉ ካልተስማሙበት ሂልተን ለብቻው የሚፈጥረው ህግ የለም” ቢባልም፡ አቶ ሹምዬ አሁንም ይህንን ታግሎ ማግኘት እንዳለበት በማመን የኢትዮጵያ ሆቴሎችን አመራር እየሰበሰበ፡ ይህንን መሰረታዊ የሆነ የሰራተኞች ጥቅም ማስከበር እንዳለባቸው ሲያግባባና ሲያወያይ ለብዙ ጊዜ ከጣረ በኋላ፡ በመጨረሻ የሁሉንም ፊርማና ስምምነት በማግኘት ለኢትዮጵያ ሆቴሎች ሰራተኞች የአገልግሎት ክፍያ ህግ ሆኖ ጸድቆ በኢትዮጵያ እንዲሰራ ያደረገ አንጋፋ የሰራተኞች መሪ ነበሩ።

በሆቴሎች አካባቢ እንደ አልባሌና ከሰው በታች ይታይ የነበረው ሰራተኛ፡ በእኩልነትና በሰውነት እንደሰው እንዲታይ ያደረጉ ታላቅ የሰራተና መሪ ነበሩ። የቀን ውሎ 75 ሳንቲም ሆኖ ሰራተኛው ይበዘበዝና ይታሽ በነበረበት ሰዓት፡ ወደ ሶስት ብር እንዲያድግ የታገሉ ጭቁን ነበሩ።

አቶ ሹምዬ ተፈራ የሰራተኛው ማህበር ተወካይ ሆኖ በእስራኤል ሀገር ለ7ወር በትምህርት ላይ ቆይቶ ተመልሷል። ከተመለሰ በኋላም፡ የኢትዮጵያ ሰራተኞች ማህበር የህግ አማካሪ ከነበረው ከአቶ ግርማቸው ለማ ጋር ምክትል ሆኖ የሰራና በሐረር፣ በሸዋና በጅማ ጠቅላይ ግዛቶች በመዘዋወር ሰራተኞችን በማህበር በማደራጀት የገለገለ ኢትዮጵያን አብጥርጥሮ የሚያውቅ፡ ተተኪ የሌለው አደራጅና ታጋይ መሪ ነበር። አቶ ሹምዬ ተፈራ የመጀመሪያው የኢትዮጵያ ሰራተኞች ማህበር አመራር ከነበሩት ከእነ አቶ አበራ ገሙ ጋር የሰራ ባለ ክቡርና ታላቅ ታሪካዊ ሰው ነበር።

አቶ ሹምዬ ተፈራ ቆራጥ ደፋርና ሀሳቡን በልበ ሙሉነት ሚናገርና ለቆመለት አላማ ህይወቱን ለመሰዋት ቅንጣት ታክል እንኳ ቅር የማይለው ሰው እንደሆነ የተጓዘባቸው የትግል ታሪኮች ህያው ምስክር ናቸው። ተለጣፊ መምህራን ማህበር፡ ተለጣፊ ሲኖዶስ፡ ተለጣፊ ሰራተኛ ማህበር ዛሬ በኢህአዴግ የጀመረ ይመስለን ይሆናል። ያኔም ነበር። አንድ ግዜ እንዲህ ሆነ። ደርግ የሰራተኛውን የሙያ ማህበር ኢ.ሰ.አ.ማ.ን በአዋጅ ዘግቶ በምትኩ የራሱን ተለጣፊ የሙያ ማህበር ለማቋቋም ሲል በሊቀመንበሩ መንግስቱ ኃይለማሪያም ትእዛዝ፡ 120ዎቹ የደርግ ተወካዮች በተገኙበትና በብሄራዊ ሸንጎ አዳራሽ በተጠራው የሰራተኛው ማህበር ተወካዬች ስብሰባ ላይ፡ ሊቀመንበሩ ስብሰባውን ለውይይት ከፍተው አይናቸውን እያጉረጠረጡ ችግራቸውን እንዲያስረዱ ሲጠይቁ፡ አዳራሹ በዝምታ ተውጦ፡ በፍርሀት ተሸብቦ በነበረበት ሰአት፡ ደፋሩ ሹምዬ ተፈራ ግን፡ “ክቡር ሊቀመንበር ምንም እንኳን እናንተ የአጼውና የካቢኔው ወንበር ቢሞቃችሁም፡ እኛ ግን የፓርላማ ወንበር ለመውረስ የተወከልን ሳንሆን በአቧራ ቤታችን ተሰብስበን የሰራተኛውን ጉዳይ  እንድንወያይ ቤታችን እንዲከፈትልን ነው ጥያቄያችን።” ሲል በድፍረት የአምባገነኖቹን ቁንጮ የተጋፈጠ ሰው ነበር። በዚያ ድፍረታቸውም ልክ እንደ ንጉሱ ዘመን፡ በደርግም ጥርስ ውስጥ ገቡ። በ1967/68 ዓ.ም. የደርግ ባለስልጣናት ሊረሽኗቸው ካሰለፏቸውና ሰራተኛው እኛንም አብራችሁ ጨርሱን እንጂ አናስገድልም ብሎ በተአምር ካተረፋቸው 54 የሰራተኛ መሪዎች ውስጥ አንዱ ነበር። ያንን ሁሉ ተመልክተው ነው፡ እህታቸው ወ/ሮ አስናቀችና የትግል አጋራቸው አቶ ወልዴ ቱቶ ከዚያ እሳት ውስጠ ይወጣል ብሎ የገመተ የለም ያሉት። አቶ ሹምዬ ከዚያ ሁሉ እሳት ውስጥ ቢወጡም፡ ትግላቸው ግን ወደ ሌላ ደረጃ አደገ እንጂ ወደኋላ አላፈገፈጉም። ወደ በረሀ ገቡ።

በበረሀ፡ በሜዳው

የሰራተኛው ተወካይ በነበሩበት ግዜ ሁሉ፡ አብረዋቸው የነበሩት የትግልና የስራ ባልደረቦቻቸው እንደሚመሰክሩት፡ ሌሎች ለመናገር የፈሩትንና ያፈሩትን በልበ ሙሉነትና በድፍረት አደባባይ ወጥተው በመናገር ይታወቃሉ። ነገር ግን፡ የዘመኑ የፖለቲካ ባህል ነበርና፡ ይሄ ድፍረታቸው በንጉሱም ይሁን ከንጉሱ በቀጠለው ወታደራዊ አገዛዝ ዘንድ አልተወደደላቸውም። ጥርስ ውስጥ አስገባቸው። ስለዚህም ከ1975 ዓ.ም. ጀምሮ ለመገደል ይፈለጉ ጀመር። ስለዚህም ለሁለት ዓመት ሕቡእ ገቡ። በህቡእ በቆዩበት ሰዓትም፡ ለሞት የሚፈለጉትን በማትረፍና ወደውጭ በማስወጣት ሲያስተባብሩ ቆይተው፡ በእስቸጋሪ ሁኔታ ውስጥ አልፈዋል። ግድያው እየከፋ ሲመጣም፡ የትጥቅ ትግል ለማድረግ በ1976 መጨረሻ ወደ አሲምባ፡ በረሀ ወረዱ።

አቶ ሹምዬ፡ ሁልግዜም ቆሞ ከመሞት፡ እየታገሉ መሞትን ስለሚመርጡ ነው ወደ አሲምባም የገቡት። ለራሳቸው የግል ጥቅም ብቻ የመቆም ፍላጎት ከቶም አልነበራቸውም። ለህዝብ እንጂ። እህታቸው ወ/ሮ አስናቀች፡ በዚህ የቀብር ስነ-ስርአት ላይ የተገኙ ጓዶቻቸውም እንደሚመሰክሩት፡ ከልጅነታቸው ጀምሮ የሕዝብ ጉዳይ የሚያንገበግባቸው፡ ለሰራተኛው መብት በመታገል የልጅነት እድሜያቸውን የገፉ ሰው ነበሩ። ሰላማዊ ሰልፍ በተከለከለ ጊዜ እንኩዋን፡ ሰው እንቀብራለን ተብሎ የሀሰት የአስከሬን ሳጥን ተሸክመው፡ የአፍሪካ አንድነት ድርጅት ስብሰባን ሊያስተናግዱ ሸር ጉድ ይሉ የነበሩትን ንጉስ በማሳጣትና የሰራተኛው የመደራጀት መብት እንዲፈቀድ የታገሉና ያስታገሉ ሰው ናቸው።

በሜዳ ከሳቸው ጋር የነበሩት፡ ሌላ ወዳጃቸው የሜዳ ውሏቸውን እንዲህ ብለው ተርከውልናል። በ1976/77ወደ አሲምባ ገብተው፡ በሰራዊቱ የማሰልጠኛ ክፍል ውስጥ የሚሰጠውን ስልጠና ወስደው፡ በተለያየ እርከን በሀላፊነት ሲያገለግሉ ቆይተው፡ በ1978/79 ዓ.ም. በሰራዊቱ ላይ በሕዝባዊ ወያኔ አርነት ትግራይ/አሁን ወያኔ በምንለው በደረሰበት ጥቃት ምክንያት፡ ሰራዊቱ ቦታ ለቅቆ ወደ ቤጌምድር ሲሻገር እሳቸውም ትግሉን ለመቀጠል ወደዚያው አብረው አምርተዋል። በዚያ ሂደት ውስጥም፡ አቶ ሹምዬ ከራሳቸው አስቀድመው፡ ሌሎች የሰራዊቱ አባላት በሰላም እንዲያልፉ በማድረግ፡ የሰራዊቱን የገጠር ትግል በማስተባበር፤ የማእከላዊ ትጥቅና ስንቅ አቅርቦትን በማደራጀት ሲያገለግሉ ቆይተዋል። እኚሁ የትግል አጋራቸው እንደሚመሰክሩትም፡ በሰራዊቱ ውስጥ በተለያዩ ወቅቶች የሚነሱትን ችግሮች በሰላም እንዲፈቱ፡ ያላሳለሰ ጥረት ያደረጉ ታላቅ የድርጅታቸውም የአገራቸውም ሰው ነበሩ። መስዋእትነት እስከመክፈል ድረስ ተዘጋጅተው በታላቅ ትጋትና አንክሮ ለትግሉ አስተዋጽኦ ሲያደርጉ የነበሩ ታጋይ ናቸው። ሰራዊቱ ላይ ተደጋጋሚ ጥቃት ሲደርስበት ለሌሎች የመዳንን ቅድሚያ ሲሰጡ ቆይተው፡ ሰራዊቱ በ1982 ወደ ሱዳን ተሰዶ በገባ ግዜ፡ እሳቸውም ከስድስት ዓመት ትግል በኋላ ወደ ሱዳን ተሰደዱ። በሱዳንም አላረፉም። ከድርጅታቸውና ከሌሎች የሰራዊቱ አባላት ጋር ለትግሉ አስተዋጽኦ ሲያደርጉ፡ እንዲሁም በስራ በመሰማራት ኑሮዋቸውን ሲረዱ ቆይተው፡ በ1983/84 ዓ.ም. ወደ ቫንኩቨር/ካናዳ መጡ።

ደግሞ ወዲህ ወደካናዳ፡ ወደምእራቡ

ምናልባት፡ በቅርብ ግዜ ለመጣን ሰዎች ካልሆነ በስተቀር፡ ላለፉት 25 ዓመታት፡ በቫንኩቨር፡ በካናዳ እና በሰሜን አሜሪካ የኢትዮጵያ ማህበረሰብ ውስጥ ሲያበረክቱ የኖሩትን አስተዋጽኦ መዘርዘር ለቀባሪው ማርዳት ይሆንብናል። ይሁን እንጂ፡ ለታሪክ ተመዝግቦ እንዲቀርና፡ እንዳይረሳም ጭምር፡ ጥቂቱን ልናወሳ እንሻለን። በቫንኩቨር ውስጥ የኢትዮጵያ ማህበረሰብ ለመጀመሪያ ግዜ እንዲቋቋም በማድረግ፡ ማህበረሰቡ ከመንግስት ፈንድ እንዲያገኝና ቢሮ አቋቁሞ ሶስት ሰራተኞች ቀጥሮ እንዲያንቀሳቅስ በማድረግ የሰሩ የማህበረሰቡ መስራችና መሪ ናቸው። ከዚያ ግዜ ጀምሮ፡ በሞት እስከተለዩባት እለት ድረስ በህመማቸው ወቅት እንኳን ከማህበረሰቡ አልተለዩም። የኢትዮጵያ ስም በተጠራበት ቦታ ሁሉ ጋሽ ሹምዬ አሉ። አሁን በስልጣን ላይ ባለው ስርአት ንጹሀን ወጣቶች በተለያየ ሰዓት ሲገደሉ፡ ተቃውሞን ለመግለጽ በሚጠሩ ሰላማዊ ሰልፎች ላይ ሁሉ ግንባር ቀደም ሆነው፡ ያለኩራትና ትእቢት፡ ይልቅስ በትህትናና በቁጭት፡ መፈክር በማንገብ፡ መፈክርም በማሰማት፡ ከሮብሰን፡ አደባባይ እስከ አሜሪካን ኤምባሲ፡ ከቫንኩቨር ሰን እስከ ሲቢሲ የተሰለፉ፡ የማይደክማቸው፡ የኢትዮጵያ እጣ ፈንታ ሁሌም የሚያስጨንቃቸው፡ የሚያንገበግባቸው ታላቅ ኢትዮጵያዊ ናቸው። እስከ እለተ ሞታቸው ድረስ፡ የኢትዮጵያ ፍቅር እያቃጠላቸው፡ ህመማቸው እንኳን ሳይገታቸው በኢትዮጵያዊያን መድረክ ላይ መገኘታቸውን መስክረናል። ባለፈው የፈረንጆቹ ነሀሴ ወር፡ በኢትዮጵያ በድርቅ ለተጎዱ ሰዎች በተዘጋጀ የገንዘብ ማሰባሰቢያ ምሽት ላይ፡ ብዙዎች በሚያሳምንም በማያሳምንም ምክንያት ሳይገኙ ሲቀሩ፡ እሳቸው ግን እዚያ ነበሩ። ባመኑበት ዓላማ፡ እስከመጨረሻው ድርጅታቸውንም፡ አገራቸውንም እንዳገለገሉ፡ ለራሳቸው፡ ለህዝባቸው፡ ለአገራቸው እና ለድርጅታቸው እንደታመኑ፡ እስከመጨረሻውም

በእምነታቸው ጸንተው፡ በተወለዱ በስልሳ ስድስት ዓመታቸው፡ ከአገራቸው በወጡ ደግሞ በ33 ዓመታቸው ከዚህ ዓለም በሞት ተለይተዋል። አቶ ሹምዬ ቤተሰባቸውን አጥብቀው የሚወዱ፡ የአራት ልጆች የያሬድ የሲራክ የዮዲት እና ቅዱስ አባት ናቸው።

እንደ ማሳረጊያ፡ እንደ አስተያየት

የሕይወት ክፋቷ፡ የሰው ልጅ ገድሉ፡ የሰው ልጅ መልካም ስራው፡ የሰው ልጅም ለሰው ልጅ ያደረገው መልካም ነገር ጎልቶ የሚወጣው፡ ከዚህ ዓለም በሞት ሲያልፍ ነው። የስደት ክፋቱም ደግነቱም እኩል ያደርጋል። አቶ ሹምዬ በመካከላችን፡ እንደተራ ሰው ሲመላለሱ፡ እንደ እኩያና እንደ አዋቂ ስከራከራቸው፡ ስነነተርካቸው፡ አንድም ቀን ግን ከጭቁን ቤተሰብ ተወልደው፡ ከልጅነታቸው አንስቶ ለዚህ ጭቁን ህዝብ ሲታገሉ መቆየታቸውን፡ ከአቃቂ በሰቃ እስከ ሂልተን ሆቴል፡ ከአሲምባ እስከ ቤጌምድር፡ ለኢትዮጵያዊያን ነጻነትና መብት መታገላቸው አንድም ቀን ውል ብሎብን አያውቅም። አቶ ሹምዬ ተፈራ ኦሮምኛ፡ አማርኛ እንግሊዘኛ አቀላጥፈው የሚናገሩ፡ የኢትዮጵያን ክፍለ ሀገራት፡ ከሰሜን እስከ ደቡብ አሳምረው የሚያውቁ፡ አቶ ጥጋቤ እንደገለጣቸውም፡ "በማተቡ፡ ከእምነቱ ፈቀቅ ሳይል የሞቱ ንጽህ ኢትዮጵያዊ" ናቸው። የአቶ ሹምዬ ሞት በማህበረሰባችን ውስጥ የሚያመጣውን ጉድለት ለመረዳት፡ ብዙ መቆየት አያስፈልገንም። ከንግዲህ ሰልፍ የሚሰለፈው፡ መፈክር የሚያሰማው፡ ስለኢትዮጵያዊያን ጭቁኖች የሚሟገተው ሹምዬ በመካከላችን የለም። ስራውና ታሪኩ ግን ለዘለዓለም ከኛ ጋር ይኖራል። ፈታሪ ነፍሳቸውን በገነት እንዲያኖር እንማጸናለን። ለአቶ ሹምዬ ቤተሰቦችና ወዳጆቻቸውም መጽናናትን እንመኛለን።